# የ“ሂዩማን ራይትስ ዎች” ገመና ሲፈተሽ

**ዘአማን በላይ**

bzaman@yahoo.com

በሚያነሳቸው ኢትዮጵያ-ነክ ጭብጦች በርካታ ሀገር ወዳድ ዜጎች የተባ ብዕራቸውን ከአፎቱ መዘው ሃሳባቸውን እንዲሰነዝሩ የሚያደርገው አይጋ ፎረም ድረ-ገፅ ከመሰንበቻው “የሰብዓዊ መብት ዋጋው ስንት ነው?” የሚል ዘገባን አስነብቦን ነበር። የፅሑፉ ባለቤት የሆኑት አቶ ሄኖክ ሳሙኤል በመጣጥፋቸው ምናልባትም ብዙ አፎች፣ ነገር ግን መስሚያ አልባ ስለሆነውና ራሱን “ሂዩማን ራይትስ ዎች” እያለ የሚጠራውን አክራሪ ኒዩ-ሊበራል ድርጅትን ማንነትና በሀገራችን ላይ የሚፈፅማቸውን ደባዎች በማስረጃ አስደግፈው በጥሩ ሁኔታ ዳስሰውታል። እነሆ ባሉበት ቦታ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።…

በሰብዓዊ መብት ጃኖ ተጀቡኖ፤በየሀገሩ ኒዩ-ሊበራሊዝምን በኃይል ለማስፈን የሚፈረፈጠው ይህ ድርጅት ከተቋቋመበት ባህው ጋር ፈፅሞ የማይገናኙ ተግባራቱ ስፍር ቁጥር የላቸውም። ታዲያ እኔም “ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም” እንዲል የሀገራችን ሰው፤ ቅሌቱ የተራራ ያህል የተቆለለውን የዚህን ተቋም ህልቆ መሳፍርት የሌለውን ገመና ላወጋችሁ ብዕሬን ከወረቀት ጋር እንዲህ አገናኘሁት። መልካም ንባብ።…

በተቋሙ ዙሪያ ጥናት ባደረጉ ተመራማሪዎች ዘንድ “የሰብዓዊ መብቶች መመሪያዎችን የሚጥስ ነው” የሚባለው ሂዩማን ራይትስ ዎች፤ የተመሰረተው እ.ኤ.አ. በ1978 ዓ.ም በሚል ስያሜ ነበር። ወቅቱ ዓለም በምዕራቡና በምስራቁ ጎራ የተከፋፈለችበት ጊዜ ስለነበር፤በያኔዋ ሶቭየት ህብረት የሚመራውን የምስራቁን ጎራ ለማዳከም ራሳቸውን “የኢምፔሪያሊዝም ወኪሎች” እያሉ በሚጠሩ የሊበራሊዝም አቀንቃኞች እንደተቋቋመ በድርጅቱ ዙሪያ የተፃፉ ድርሳናት ያወሳሉ።ኋላ ላይም ተቋሙ “የሂዩማን ራይትስ ዎች የአውሮፓና የኤስያ አማካሪ ኮሚቴ” ወደሚል ስያሜ ተቀይሮ “ፎርድ ኮርፖሬሽን” ከተሰኘ ኩባንያ በተገኘ 400 ሺህ ዶላር የመነሻ ገንዘብ ሊቋቋም መቻሉን አጥኚዎች ይገልፃሉ።

እዚህ ላይ ቁም ነገሩ ሂዩማን ራይትስ ዎች ባሻው ስም መመስረቱ አሊያም አለመመስረቱ አይደለም። ዋናው ነገር ‘ይህ ተቋም ለምን ዓላማ ተመሰረተ?’ የሚለው ወሳኝ ጥያቄ ነው። እርግጥ የያኔው “ሄልሲንኪ ዎች” በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የሶሻሊዝሙን ጎራ ለማጠልሸት የተጫወተው ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ፤ተቋሙ ዓለምን በኒዩ-ሊበራል አምሳያ ለመቅረፅና ለእርሱ ብቻ የምትመች እንድትሆን ለማድረግ ሁሉንም ዓይነት ማስገደጃዎችን በመጠቀም መጮህ ዋነኛ መለያው ሊሆን ችሏል።

እናም በሎይድ አርክዎርዚ ሊቀመንበርነትና በማሪያ ፒንቶ ካውፍማን ምክትልነት እየተመራ፤ በትክክለኛም ይሁን በተሳሳተ መንገድ የራሳቸውን አቅጣጫ መከተል የጀመሩ ሀገሮችን በሰብዓዊ መብት ስም ጎራውን እየዞረ ከኃይል እርምጃ ጀምሮ በሀገራቱ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የቀለም አብዮት እስከ ማቀጣጠል ድረስ መንከስን ብሎም በሃሜት መቦጫጨቅን ስራዬ ብሎ ተያይዞታል።

አዎ! ማንም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ “ሂዩማን ራይትስ ዎች” የሰብዓዊ መብት መርሆዎችን እየጠራ ቢለፍፍም ፤ ዓላማው ክቡሩን የሰው ልጅ መብት ማስከበር አለመሆኑን መገንዘቡ አይቀርም። ምክንያቱም በየትኛውም መስፈርት ቢሆን የራስን ፖለቲካዊና ርዕዮተ-ዓለማዊ አጀንዳን አንግቦ የሰውን ህይወት የሚቀጥፍ የቀለም አብዮት አቀጣጥሎ ዳር በመቆም እሳቱን መሞቅ ከሰብዓዊ መብት መርሆዎች ጋር የሚጣረስ በመሆኑ ነው።

ለዚህም ነው ሚስተር ማይክል ባርከር የተባሉና በግለሰብ ደረጃ በጉዳዩ ላይ ምርምር የሚያደርጉ ሰው ተቋሙን አስመልክተው በመጣጥፋቸው ሌሎች ፀሐፍቶችን በመጥቀስ “…ሂዩማን ራይትስ ዎች ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብቶች ቆሜያለሁ ቢልም፤ግንኙነቱ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ከሆኑ ተቋማት ጋር መሆኑን ያወቀው ዘግይቶ ነው።…” ያሉት። እርግጥም ተቋሙ ምንም እንኳን “በኢምፔሪያሊዝም ወኪልነት” የተሰለፈ ቢሆንም፤ ቁርኝቱን ዴሞክራሲን ከማያውቁ፣ ነገር ግን ስለዴሞክራሲ ከሚዘምሩ ኃይሎች ጋር በማድረግ የጥቂት ግለሰቦች ኪስ ማደለቢያ መሆኑን የሚመሰክሩ በርካታ ናቸው።

ከዚህ አኳያ ምርምር ያደረጉ ምሁራን እንደሚገልፁት፤ ሂዩማን ራይትስ ዎች በራሱ መንገድ የሚከተለውን “የውህዳን ዴሞክራሲን” ለማስተዋወቅ የቆመ እና በሰብዓዊ መብት ሽፋን መሪዎቹ ከእነ ጆርጅ ሶሮስ የሚያገኙትን በመቶ ሚሊዩን የሚቆጠር ረብጣ ዶላር

ላለማጣት የሚወራጭ ተቋም ነው። ታዲያ ይህን ዕውነታ ሚስተር ጁሊ ሜርትስ የተባሉ ፀሐፊም ይጋሩታል። በእርሳቸው አባባል በሰብዓዊ መብት ዙሪያ የሚካሄዱ ተግባሮች፤ ከመብቶቹ ባህሪያት ጋር አብረው የማይሄዱ፣ መንታ አቋም ያላቸው፣ከግልፅነት ይልቅ የሰውን ልጅ ተፈጥሮ ፍርሃት የሚያላብሱና ለአጭር ጊዜ በመሳሪያነት የሚውሉ ናቸው። ታዲያ እዚህ ላይ ልብ ይሏል– የሚስተር ሜርተስ አገላለፅ ሂዩማን ራይትስ ዎችንና ከጀርባው ሆው የሚጋልቡትን "ቹ!" ባይ ፅንፈኛ ኒዩ-ሊበራል ኃይሎች  የተሸከሙትን ድብቅ ዘንቢል አራግፎ የሚመለከት መሆኑን።

እርግጥም የዓለም ህዝቦችን "እኔ የምከተለውን ፖለቲካዊ- ኢኮኖሚ እምነት በግድ ዋጡ" ማለት የሰብዓዊም ሆነ የዴሞክራሲያዊ መብት ባህሪያዊ እሳቤ አይደለም። በአንድ ፅንፍ "የሰብዓዊ መብት ተሟጋች" የሚል የውሸት ስያሜን አንግቦ ፣በሌላኛው ወገን ደግሞ የሰውን ልጅ ሰብዓዊ መብት አፍኖ ለመያዝ በመንታ ምላስነት መቋመጥ ከመብቱ ጋር የሚያያይዘው አንዳች ምክንያት የለም።

የሰው ልጅ ተፈጥሮን በግብዓትነት እየተጠቀሙ፣ መልሶ  እርሱኑ በቀለም አብዮት ወደ ሰቀቀንና ስጋት ውስጥ ለመክተት መጣር ፀረ-ሰብዓዊ መብት እሳቤ ነው። እናም በማንኛውም ሰብዓዊ ሰው ዕይታ ሂዩማን ራይትስ ዎች የሰብዓዊ መብት ተናዳፊ ተርብ መሆኑ አሌ የሚባል ሃቅ አይደለም። አዎ! ተቋሙ በውስጡ ለሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች ሲል በክቡሩ የሰው ልጅ መብት ላይ እንደ እባብ ከመጠምጠም ወደ ኋላ የሚል አይደለም። ታዲያ ይህን ዕውነታ ዘርዝሮ መመልከቱ ጠቃሚ ነው።...

ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ተመራማሪዎች እንደሚገልፁት፤ሂዩማን ራይትስ ዎች የትርፍ ማጋበሻ የሆነውን አጀንዳ ለማሳካት ሲል የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። እርግጥም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መድረክን በመሰሉ "ሆድ-አደር" ተቃዋሚዎች አማካኝነት የቀለም አብዮት ለማቀጣጠል ይጥራል፣ ዴሞክራሲን ተፃርሮ በሰው ሀገር በማን አለብኝነት ጣልቃ በመግባት ለእርሱ አፋሽ-አጎንባሽ የሆኑ ኃይሎችን "ዙፋን አንጋሽ" ለመሆን ይሞክራል። ይህ ካልተሳካም የፈጠራ ሪፖርትን እንደ ልብ ወለድ በመድረስ በእርሱ የአስተሳሰብ መዘውር በሚሽከረከሩት የምዕራቡ ሚዲያዎች አማካኝነት በዘመቻ መልክ  የውሸት ጋጋት እሩምታውን ያንጣጣል። እርግጥ ከእነዚህ ተግባራቱ መካከል ጥቂቶቹን ለአብነት ያህል ማንሳት የተቋሙን ማንነት አብጠርጥሮ ለማወቅ ያግዛል።

የሂዩማን ራይትስ ዎች አደገኛው እንቅስቃሴ በሰብዓዊ መብት ሽፋን በየሀገራቱ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት ነው። ኸርማን ፣ ፒተርሰን እና ዛሙሊ የተባሉ ፀሐፍት እ.ኤ.አ. በ2007 "ሂዩማን ራይትስ ዎች ጦረኛን በማገልገል ተግባር ላይ" በሚል የትችት ጥናታቸው፣ ፅንፈኛው ተቋም ለቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ መበታተን ወሳኝ ሚና እንደነበረው አትተዋል። በእነርሱ የጥናት ግኝት "ለሰብዓዊ መብት ቆሜያለሁ" የሚለው ተቋሙ በዩጎዝላቪያ ውስጥ ሰብዓዊ መብትን በመጣስ ረገድ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነበር። በዚህም በሀገሪቱ ውስጥ የተቀሰቀሰውን የእርስ በርስ ግጭት እንደ ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም እ.ኤ.አ. ከ1992 ጀምሮ ሰብዓዊ መብቶች የሚጻከሙበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት እንዲሁም በወቅቱ የሰሜን ቃል ኪዳን አባል ሀገራት ጦር (ኔቶ) በሀገሪቱ ላይ የፈፀመውንና "ከፍተኛ ዓለም አቀፍ ወንጀል" የሚባለውን ተግባር እንዲያከናውን መደላድል መፍጠሩን በምሬት ይገልፃሉ።

የአክራሪ ተቋሙ ፀረ-ሰብዓዊ መብት ተግባራት በዚህ ብቻ የተገቱ እንዳይመስላችሁ። ነገረ-ስራው "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" እንዲሉት በመሆኑ፣ በዩክሬንም "ብርቱኳናማ አብዮት" በማቀጣጠል እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ሰዎች ለህልፈተ-ህይወት እንዲዳረጉ በማድረግ እኩይ ሴራውን ከውኗል። እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ይመስለኛል– ፈረንጆቹ "adding fire into the fuel" የሚሉት– "በእሳት ላይ ቤንዚን ማርከፍከፍ" እንደማለት።

ያም ሆነ ይህ ፣የድርጅቱ ዓላማ አክራሪ የኒዩ- ሊበራል አስተሳሰብ ያናወዛቸውን "ዲታውን" ጆርጅ ሶሮስ ዓይነት ግለሰቦችን ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ፍላጎት ማርካት በመሆኑ፣ የቀለም አብዮትን በዚምባባዌና በኬንያ እንደ ገፀ-በረከት በማቅረብ የሰዎች ደም በከንቱ እንዲፈስ በተባባሪነት መሰለፉን መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህ ተግባሩም አሻንጉሊት መንግስት ለመመስረት ጥረት ማድረጉ የአደባባይ ምስጢር ነው– ምንም እንኳን በእነዚህ ሀገራት ሴራው እርሱ እንደፈለገው ሙሉ ለሙሉ ባይሳካለትም።

"ዓለምን የሚያዋጣት ኒዩ-ሊበራሊዝም ነው፣ከዚህ ውጪ የራሳችሁን መንገድ የምትከተሉ መንግስታት ወዬሁላችሁ!" በሚል ቃና "የምፅዓት ቀን" መልዕክቱን በተዘዋዋሪ መንገድ ማስረፅ ብሎም ዓለምን በአንድ ዋልታ (uni-polar) እሳቤ ለመምራት የሚከጅለው ይህ ቡድን፣የቀለም አብዮት ካልተሳካለት ከሌሎች የርዕዮተ-ዓለሙ አቀንቃኞች ጋር

በመተጋገዝ የውሸት ሪፖርትን እንደ በረዶ በሀገራቱ ላይ በማዝነብ ላንቃው እስኪደርቅ መጮህ ሁነኛ ተግባሩ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በተለይም እነ ጆርጅ ሶሮስ ከሚመሩበትና "ሁሉንም ነገር ለገበያውና ለባለሀብቱ መተው አለበት፤መንግስት ህግና ስርዓትን ከማስከበር ባለፈ፣ ኢኮኖሚው ውስጥ እጁን ማስገባት የለበትም " ከሚለውና ለመንግስት "የዘበኝነት" ሚና ከሚሰጠው ከስሮ እርቃኑን ከወጣው ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ፍልስፍና ውጭ በራሳቸው መንገድ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ላይ የሚሰነዝረው የቅጥፈት አሉባልታ እጅግ የሚያስገርም ነው። ይህንን ዕውነታ ሩቅ ሳንሄድ በማደግ ላይ ከሚገኙት ቻይና እና ኢትዮጵያ አኳያ መመልከት ይቻላል።

እንደሚታወቀው ቻይና ከኒዩ-ሊበራሊዝም ውጭ የሆነና ለራሷ የሚበጃትን ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ መስመር ቀይሳ መጓዝ ከጀመረች ጥቂት አስርታት ተቆጥረዋል። በዚህም የሀገሯን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ አስወንጭፋለች። በጥቂት ዓመታት የዕድገት ግስጋሴዋም የዓለምን ሁለተኛ የኢኮኖሚ ማማን ልትቆናጠጥ ችላለች። በጣት በሚቆጠሩ አስርታትን እልፍ ካለች ደግሞ የልዕለ ኃያልነቱን ቦታ ከአሜሪካ ልትረከብ እንደምትችል ትንበያዎች ይጠቁማሉ። ይሁንና ከቀዝቃዛው ጦርነት ፍፃሜ በኋላ የሀገሪቱን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ግስጋሴ ለማላሸቅ፤አንዴ በዴሞክራሲ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሰብዓዊ መብት ስም ከሌሎች ፅንፈኛ ኒዩ-ሊበራሊስቶች ጋር በመሆን ያሉና የሌሉ አሉባልታዎችን በመንዛት እንደ ወገብ ምንትስ ሊላቀቃት አልቻለም–ጉደኛው ሂዩማን ራይትስ ዎች።

ቋሚ አጀንዳውን የተለየ ፖለቲካዊና ርዕዮተ-ዓለማዊ ፍልስፍና የሚከተሉ መንግስታትና ህዝቦችን በማጥላላት ላይ የመሰረተው አክራሪ ተቋሙ፤እንደ ሌሎች ሀገራት ሁሉ ለቻይናም ያልሰጣት "የዳቦ ስም" አለ ለማለት አይቻልም። ሆኖም የቻይና ህዝቦችና መሪዎቿ የሂዩማን ራይትስ ዎችን የቁራ ጩኸት "ጆሮ ዳባ ልበስ" በማለት ሰምተው እንዳልሰሙ በመሆን ልማታቸውን በማፋጠን ላይ ማተኮርን መርጠው ታላቅ የዕድገት ድል ማስመዝገብ ችለዋል።

በዚህ ብልህ ውሳኔያቸውም አስፈላጊ ሲሆን ለኒዩ-ሊበራሎቹ ምላሽ እየሰጡ የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎችን ጩኸት ጭው ባለ በረሃ ላይ እንደተዘራ እህል መክኖ እንዲቀር ማድረግ ችለዋል። ዳሩ ግን ምን ያደርጋል?!– ሂዩማን ራይትስ ዎችና በአምሳያው የተፈጠሩት አጫፋሪ ሚዲያዎቹ በደረሰባቸው የኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ከቻይና እየተበደሩ፣

መልሰው በተፃራሪ መልኩ እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ ለልማት ታታሪ በሆነችው ሀገርና በህዝቦቿ ላይ የመዘዙትን የፅንፈኝነት ሰይፍ ወደ ሰገባው ሊመልሱት አልቻሉም።

እናም በቻይና ከተካሄደው ኦሎምፒክ በፊት በቲቤት የግዛት ጥያቄ ሽፋን የተቀሰቀሰውን "የክሪምሰን አብዮት" በማቀጣጠል ሂዩማን ራይትስ ዎችና መሰሎቹ ጉልህ አሉታዊ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን በመስኩ ጥናት ያደረጉ ወገኖች ያስረዳሉ። ይህ ሁኔታ ግን ያቺን ሀገር ከልማት ግስጋሴዋ የኋሊት ሊያንሸራትታት አልቻለም። ይልቁንም የዓለምን በትረ-ኢኮኖሚ ለመጨበጥ ብርታት የሆናት ይመስላል። እርግጥም "ውሾቹ ይጮሃሉ ፤ግመሎቹ ግን ጉዟቸውን ቀጥለዋል" የሚለውን ይትበሃል ይህ የቤጂንግ ተግባር በሁነኛ ማሳያነት ሊገልፀው የሚችል ይመስለኛል።

አዎ! ሂዩማን ራይትስ ዎች በሰብዓዊ መብት ስም ትርፍ የሚያጋብስ "ሲራራ ነጋዴ" በመሆኑ፤ ትርፉን ሊያጓድልበት የሚችለውን ነገር ከሀገራት አንፃር ማስላቱ የግድ ነው። በተለይም የአፍሪካን ጥሬ ሀብት "ሁሉም ነገር ለገበያው መተው አለበት" በሚል የከሰረ ፈሊጥ እንዴት አድርጎ በኒዩ-ሊበራል "ዲታዎች" እያዘረፈ ስራ ማስኬጃ እንደሚያገኝ "የሒሳብ ማባዣ ማሽኑን" ይዞ መራወጡ የሚደንቅ ጉዳይ አይደለም።

ምክንያቱም በመላ አህጉሪቱ ላለፉት 30 እና 40 ዓመታት በዚህ መንገድ ያሻውን ሲፈፅም የነበረ በመሆኑ ነው። ግና ትናንት ዛሬ አይደለም። አፍሪካውያን በእነዚያ የጨለማ ዓመታት ኒዩ-ሊበራሊዝም የኢኮኖሚ ቀውስን ከማባባስ፣ጥገኝነትን ከማጠናከር፣የልማት ተስፋቸው በፅልመት እንዲዋጥ ከማድረግ ውጭ የፈየደላቸው አንዳች ነገር አለመኖሩን በአያሌው ተገንዝበዋል።

በእነዚያ ዓመታት ያለ ውዴታቸው በግዴታ እንዲለብሱት የተደረጉት በኒዩ-ሊበራሊዝም ልክ የተሰፋ የተንከረፈፈ ሸማን አውልቀው በመጣል፤ ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አብሮ ሊሄድ የሚችል ልከኛ የአስተሳሰብ ልብስን መደረብ ከጀመሩ ሰነባብተዋል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በበሳል፣ብቃት ባለውና በአርቆ አሳቢ መሪ የሚመሩ ሀገራትም፤ ከነባራዊ ሁኔታቸው በመነሳት በነደፉት የልማት ስትራቴጂ አማካኝነት በአማካይ ከ10 በመቶ በላይ በተከታታይ ማደግ መጀመራቸውም ከኒዩ-ሊበራሊዝም ውጭ ሌላ አማራጭ መኖሩን በገሃድ የሚያመላክት ዕውነታ ነው።

ነገር ግን በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ ብቻ "ከእኛ ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ እሳቤ በስተቀር ሌላ አማራጭ ላሳር ነው" እያሉ የሚመፃደቁትን የገበያ አክራሪዎች የሚወክለው ሂዩማን ራይትስ ዎች ይህ የሀገራችን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት የእግር እሳት ሆኖበታል። ለዚህም በዋነኛነት የሚጠቀሰው ምክንያቱ 'ኢትዩጵያ ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ምሳሌ በመሆን፣ሌሎችም ይህን አቅጣጫ ተከትለው ስለሚያድጉ ጥቅማችን ሊነካ ይችላል' ከሚል ስጋት የመነጨ ነው። በዚህም ሳቢያ ከረዘመ በየስድስት ካነሰ ደግሞ በየሁለት ወሩ የውሸት ድርሳንን እንደ "አቡነ ዘ-በሰማያት" ማነብነብ ስራዬ ብሎ ተያይዞታል።

ምንም እንኳን የቀለም አብዩት በኢትዩጵያ ነባራዊ ሁኔታ የሚቀሰቀስበት ምህዳር ባይኖርም ፣ያለ የሌለ ኃይሉን ከመጠቀም ወደ ኋላ የማይለው ሂዩማን ራይትስ ዎች ግን በሌሎች ሀገራት ውስጥ እንደሚያደርገው ሁሉ አሻንጉሊት ወኪሎቹን በሀገራችን ውስጥም ማሰለፉ አልቀረም። ለአብነት ያህል በምርጫ 97 ወቅት ኢትዩጵያ ውስጥ የነበሩትን የሲቪል ማህበራት ወኪሎችን በመመልመል እንዲንቀሳቀሱ ማድረጉን ማውሳት ይቻላል።

በዚህ ረገድ በወቅቱ የክርስቲያናዊ ተራድኦ ልማት ድርጅት ጥላ ስር የነበሩት እና አቶ ዳንኤል በቀለ የተባሉ የተቃዋሚ አቀንቃኝን መልምሎ ገንዘቡን በመርጨት ከተሰማሩበት የስራ መስክ ውጭ የምርጫ ተዋናይ እንዲሆኑ ማድረጉን እናስታውሳለን። ታዲያ የውጭ ኃይሎች ፀረ-አትዩጵያ ፍላጎት መጠቀሚያ መሳሪያ የሆኑት እኚህ "ሆድ-አደር" ግለሰብ፣ ባይሳካላቸውም በዚያን ጊዜ ላደረጉት አስተዋፅኦ አክራሪው ተቋም የአፍሪካ ክንፉ ምክትል ዳይሬክተር አድርጎ ሾሟቸዋል። ግና በሀገራችን ውስጥ ለእንዲህ ዓይነቱ የቀቢፀ-ተስፋ ድርጊትና ከሀዲዎች ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ ሃሳባቸው እንደ ጉም በኖ ሊቀወር ችሏል። ያም ሆነ ይህ ግን፣ፅንፈኛው ተቋም ለእኩይ ዓላማው ስኬት ምን ዓይነት ሰዎችን እንደሚመለምል ውድ አንባቢዎቼ ልብ ይሏል!....

ታዲያ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ሂዩማን ራይትስ ዎች አንድን ልማታዊ ሀገር ጠምዶ ከያዘ እየፈበረከ የሚለቀልቀው ቀለምና የሚያባክነው ወረቀት የትየለሌ ነው፡፡ በሰብዓዊ መብት ስም የሚያራምደው አጀንዳ ይታወቅበትም አይታወቅበት እርሱ ደንታው አይደለም፡፡ |የበሬ ምንጥስ ይወድቃል ብላ ስትከተል ዋለች' እንደተባለችው እንስሳ በጽንፈኛው ቡድን አጋፋሪነት ዙፋን ላይ ለመውጣት ሱባኤ የገቡት በህዝብ የተተፉ ተቃዋሚዎችም ሆኑ፣ በሻዕቢያ ተላላኪዎች የሚነዙ አሉባልታዎች ቢሆኑም ባይሆኑም እርሱ ምን ተዳው? – ለሪፖርት ፍጆታ እስከዋለለት ድረስ በመርዝ በተለወሱ ቃላት ታጅቦ

ከመለፍለፍ እና ከማስለፍለፍ ወደኋላ አይልም፡፡ ከእነዚህ ወገኖች መረጃ ሲደርቅበት ደግሞ ኬንያ ውስጥ ቁጭ ብሎ በተባራሪ ወሬ የሐገራችንን ልማት በማጣጣል ጥናት አጠናሁ እያለ ሪፖርት ያወጣል፡፡ ‵ሂዩማን ራይትስ ዎች አበደ እንዴ?′ እስኪባል ድረስ ከጳጳሱ ቄሱ እንዲሉት አይነት ሆኖ ድንበር በመሻገር ለኢትዮጵያ ህዝብ አዛኝ ቅቤ አንጓች ሆኖ ያላዝናል፡፡

እስቲ ውድ አንባቢዎቼ የጠራ ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ የአክራሪ ተቋሙን ተራና መሰረተ-ቢስ ውንጀላዎች በጥቂቱም ቢሆን እየነቀስኩ ላውጋ፡፡ የሚያገኛቸውን መረጃዎች ሆን ብሎ በማጣመም ተራ የፖለቲካና የርዕዮተ-ዓለም ትርፍ ለማግኘት የሚሻው ይህ ፅንፈኛ ቡድን ‵በኦጋዴን ባልታወጀ ጦርነት የጅምላ ጭፍጨፋ እየተካሄደ ነው′ በማለት ያወጣው የውሸት ሪፖርት ‵ቁጥር አንድ ፕሮፖጋንዳ′ ተብሎ ሊመዘገብ የሚችል ነው፡፡

ይሁንና ይህንን የሻዕቢያ ተላላኪ የሆነውን የኦብነግ ዘገባን ተንተርሶ ያቀረበው የፈጠራ ልብ ወለድ በወቅቱ በተደረገው ማጣራት እርቃኑን ሊቀር ችሏል፡፡ ምንም እንኳን እንደተለመደው የጽንፈኛውን ቡድን የቅጥፈት ሪፖርት እነ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሲ.ፒ.ጄ. እና ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕን በመሳሰሉ አክራሪ ኒዮ ሊበራል ኃይሎች የደቦ ዘመቻ ሊደገፍ ቢፈለግም ፣ እውነታው ሲጣራ ‵ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ′ እንዲሉት አይነት ሆኖ ነው የተገኘው፡፡

በወቅቱ ሂዩማን ራይትስ ዎች ‵የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ቤት አቃጠለ፣ሰዎች ገደለ…ወዘተ′ የሚሉ የፈጠራ ድርሰትን ቀምሮ ቢለፍፍም ሁኔታው በገለልተኛ ወገን በተጣራበት ወቅት ተቃጠለ የተባለው ቤት በቦታው መገኘቱን እንዲሁም ‵ተገደሉ′ የተባሉ ሰዎች በህይወት እያለን የሚያሚርትብን ማነው? ማለታቸው የተቋሙ ሪፖርት በምናብ የተፈጠረ የማጥላላት ዘመቻ መሆኑን ዓለም ተረድቶታል፡፡ ተቋሙ ግን ዓይኑን በጨው የታጠበ በመሆኑ፣ ራሱን ለሌላ ውንጀላ ከማዘጋጀት አልተቆጠበም፡፡ እናም በየዓመቱ የቤተክርስቲያን ስዕለት ያለበት ይመስል የውንጀላ መዓቱን ከማዝነብ አልቦዘነም፡፡

በተለይም በምርጫ 2002 መባቻና ዋዜማ ወቅት ኢ-ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እየዘበራረቀ ‵አንድ መቶ ግፊት ማድረጊያ መንገዶች፣ እርዳታ ለፖለቲካ ፍጆታ እየዋለ ነው…ወዘተ′ የሚሉ አሉባልታዎችን ከተስፈኛ ጨለምተኛ ተቃዋሚዎች በመቃረም ትዝብት ላይ የሚጥለውን አሳፋሪ ሪፖርት አውጥቷል። ዳሩ ግን ይህ የተለመደ የፈጠራ

ልቦለድም በተጨባጭ ያለውን ሁኔታ የማያመላክትና ማስረጃ የሌለው መሆኑን፤የኢትዩጵያ የልማት አጋር ቡድን /DAG/ አጋለጠው። እርሰ ግን አሁንም |ሃፍረት ለምኔ´ ብሎ ኬንያ ውስጥ ተቀምጦ እንደለመደው ያላየውን ነገር ከመዘላበድ ወደ ኋላ አላለም።

በቅርቡም ኬንያ የሚገኙ ከፀረ - ሠላም ኃይሎች ጋር ንኪኪ ያላቸውን ወገኖች አነጋግሮ "የኢትዮጵያ መንግስት ዜጎችን በሰፈራ ሰበብ እያፈናቀለ ነው፣ በጋምቤላ ክልል አውስትራሊያን የሚያህል የቆዳ ስፋት ያለውን መሬት ለውጭ ባለ ሃብቶች ሰጥቷል" የሚል አስገራሚ ሪፖርት "የቀበሮ ባህታዊ" ሆኖ አቅርቧል፡፡ አንድ የጥናት ሪፖርት በሀገር ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ሳይመለከት፤ ናይሮቢ ቁጭ ተብሎ እንዴት ሊሰራ እንደሚችል ለማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ "ዓይንህን ጨፍንና ላሞኝህ" ዓይነት ቢሆንም፣ በዋናኛነት የአክራሪ ኒዮ - ሊበራል ኃይሉ ሳይንሳዊ ያልሆነው የስሚ ሰሚ ሪፖርት ተብዬ ከበስተጀርባው ያነገበውን ድብቅ አጀንዳ የሚያሳብቅበት መሆኑን አይስተውም፡፡ እርግጥም እውነታው ወዲህ ነው፡፡…

የኢትዮጵያ መንግስት በሀገሪቱ ያለው ጠፍ መሬት ለልማት እንዲውል እንዲሁም ለልማት ኋላ ቀር ከሆኑ ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች በተበታተነ አኳኋን ሰፍረው ስለሚገኙ በአንድነት ተሰባስበው የመሰረተ - ልማት አቅርቦቶች ተቋዳሽ እንዲሆኑ በማለም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሰፈራ ፕሮግራምን መንደፉ እርግጥ ነው፡፡

ይሁንና ሂዮማን ራይትስ ዎችና ሰሞኑን ደግሞ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ የተባለ አምሳያው የሚላዝኑት "የዜጎች ተፈናቀሉ" የሚል ጀሮ በጣሽ ቅንብር ያለው ኦርኬስትራ ውስጠ - ምስጢሩ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ይኸውም በዘመቻ መልክ የሚካሄደው የእነዚህ ኃይሎች ፕሮፓጋንዳ ርዕዮት - ዓለማዊ ዓላማን ያነገበ እንጂ፤ ከነባራዊ ሁኔታው ጋር በፍጹም የሚገናኝ አለመሆኑ ነው፡፡

ከተንሻፈፈ ኒዮ -ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ተነስቶና በስደት ላይ የሚገኙ አቅመ - ደካማ እንዲሁም ከሀገሪቱ ጠላቶች ጋር ንክኪ ወገኖች ትርኪ -ምርኪ ወሬ አንግቦ ለሪፖርት የሚያበቃው ጽንፈኛው ቡድን፤ እንደ ቅኝ ግዛት ወቅት ሁሉ ዛሬም በአፍሪካ አንጡራ ሀብት በሆነው መሬት ላይ አዛዥ -ናዛዥ መሆን ይፈልጋል፡፡ ይሁንና የአፍሪካዊያን መሬት ለህዝቦቿ የላቀ ተጠቃሚነት የሚውል መሆኑን መገንዘብ ያለበት ይመስለኛል፡፡

በኢትዮጵያም ያለው ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው በሀገራችን ለሰፋፊ እርሻ የሚውል መሬት ያለው ከሰሜን እስከ ደቡብ በሚገኘው ምዕራባዊው ክፍል ነው፡፡ ይህ ክፍል ጥቂት ቁጥር ያለው ህዝብ የሰፈረበት፣ ነገር ግን ለእርሻ ተስማሚ የሆነ ለም መሬትን የያዘ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ እንግዲህ መንግስት ይህን ሰፊ የሀብት ምንጭ ነው - ለላቀ የግብርና ዕድገት ተልም በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው፡፡

እስካሁን መልማት ከሚገባው 58 ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬት ውስጥ ለባለሃብቶች የተሰጠው መሬት 378 ሺህ ሄክታር ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ባለሃብቶችም የሀገር ውስጥና የውጭ ተብለው የተለዩ ናቸው - ቁጥራቸውም ከ26 አይበልጥም፡፡ ከእነርሱም መካከል 15ቱ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ሲሆኑ፤ አስራ አንዱ ብቻ ናቸው በውጭ ባለሃብትነት የተመዘገቡት፡፡ ለባለሃብቶቹ የተሰጣቸው መሬትም የኒዮ - ሊበራሊዝም አቀንቃኞቹ እንደሚያስወሩት ሳይሆን፤ ከአካባቢው ማህብረሰብ ይዞታ ነጻ የሆነው ተለይቶ ነው፡፡

ታዲያ እነ ሂዮማን ራይትስ ዎች ይህን እውነታ ለመስማት ባለመፈለግ፤ በራሳቸው ፍላጎት የሚያላዝኑት "እኛስ ለምን ቀረብን?" ከሚል ብስጭት ሌላ ከቶ በምንም ሊፈረጅ የሚችል አይሆንም፡፡ "በሰፈራ ምክንያት ዜጎች በጋምቤላ ክልል እየተፈናቀሉ ነው" የሚለው የአክራሪ ቡድኑ የአሉባልታ ውርጅብኝም "አያ ጅቦ ስታመሃኝ ብላኝ" ዓይነት ዓይን ያወጣ ቅጥፈት መሆኑን መሬት ላይ ያለውን ሃቅ ተመርኩዞ በመመልከት ለመረዳት አያዳግትም፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች እየተመዘገበ ካለው ዕድገት ተቋዳሽ እንዲሆኑ፤ የጋምቤላ ክልልም በ43 መንደሮች የአካባቢን ህዝብ ለማሰባሰብ ጥረት አድርጓል፡፡ ይሁንና ለእነዚህ መንደሮች ሁሉን አቀፍ የመሰረተ ልማት ተቋማትን በማሟላት ለኑሮአቸው ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችን ዘርግቷል፡፡

ይህም የመንግስት ዓላማ ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ለማድረግ መሻቱን እንጂ፤ እነ ሂዮማን ራይትስ ዎች እንደሚያስወሩት "ህዝቡን ለማፈናቀል" አይደለም፡፡ ምንም እንኳን አክራሪ ቡድኑ "ከባለቤቱ በላይ ያወቀ ቡዳ" በመሆን የባጥ የቆጡን ቢለፍፍም የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ለቁራ ጩኸቱ ቦታ መስጠት የሚገባቸው አይመስለኝም፡፡

እርግጥም ውሻው ሺህ ጊዜ ቢጮህም የበረሃው አልሚ ግመሎች የዕድገት ግስጋሴያቸውን አጠናክረው መቀጠልን ጠንቅቀው ያውቁበታል፡፡

ውድ አንባቢዎቼ የሰውን ልጅን ተፈጥሮአዊ መብት ለራሱ ስውር ዓላማ የሚያውለው ሂዩማነ ራይትስ ዎች ገመናን ዘርዝሮ መግለጽ ማለት ዓባይን በጭልፋ ሳይሆን በማንኪያ የመጨለፍ ያህል ነው፡፡ ትናንት "ሄልክንኪዎች" በሚል መጠሪያ የምስራቁን ጎራ ለማጣጣል የተቋቋመው ተቋም፤ ዛሬ ደግሞ የውንጀላ ስልቱን በመቀየር በራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ለማደግ የሚታትሩ መንግስታትና ህዝቦችን ስማቸውን ለማጥፋት የማይቧጥጠው ተራራ የለም፡፡

በጆርጅ ሶርስ ገንዘብ አቅራቢነትና እርሱን ጨምሮ 40 በግልፅ የሚታወቁ አባላት ባሉትና "የተቋሙ የአሜሪካ አማካሪዎች" በሚባሉት በእነ ሮናልድ አልግራንት፣ ሮቤርቶ አልቫሬዝ፣ ሳይንቲያ ጄ. አርንሰን፣ ካርሎስ ባሶምብሪዎ፣ ፒተር ዲ.ቤል… ወዘተ. የቦርድ አባላት" ኢምፔሪያሊዝምን እንወክላለን" በማለት "ከኒዮ - ሊበራሊዝም ውጭ ሌላ አማራጭ አለ" የሚሉ ሀገራት ውስጥ ጣልቃ ገብ እጃቸውን መቼ እንደሚሰበስቡ አይታወቅም፡፡

ነገም ሌላ ቀን ነውና ርዕዮተ - ዓላማዊ አመለካከት መልስ ራሱን እየናጠው ያለው ሊበራሊዝም ሂዩማን ራይትስ ዎችን ጠልፎ ካልጣለው የውዥንብር ናዳው መቋጫ የሚኖረው አይመስልም፡፡ በዚያው ልክም ኢትዮጵያና ሌሎች ልማታዊ ሀገራት የያዙትን "ሀገር በቀል ዕድገት" የተሰኘ የነብር ጭራን ከያዙት አይለቁትም፡፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች ግን በቅሌት ላይ ቅሌት እየደመረ ድብቁን ገመናውን እንደ ብቅል ለዓለም ህዝብ በጠራራ ፀሐይ ላይ አስጥቶት የሚታይበት ጊዜ ሩቅ የሚሆን አይመስለኝም፡፡ እስከዚያው ግን ቸር እንሰንብት፡፡